# በተለያየ ባሕል ውስጥ በስነ ልቦናዊ ቁስልና ተያያዥ ጭንቀት ላይ በሚካሄዱ ጥናቶች ውስጥ ፆታ እና ስርዓተ-ፆታ



## ፆታ እና ስርዓተ-ፆታ ከምዕራባውያን አንፃር፦

- ፆታ አንድ ሰው በተፈጥሮ ያገኘው ስነ ሕይወታዊ እና ዘረመላዊ ባሕርይ ነው።
- **ስርዓተ-ፆታ** (በእንግሊዝኛ 'ጀንደር') ስንል ሰዎች የራሳቸውን ፆታ እንዴት እንደሚረዱ እንዲሁም ፆታ ከማህበራዊ ሚናዎች እና እሴቶች ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ይገልፃል። ይህም ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ የአፍሪካ ሐገራት ህጋዊ ያልሆኑ የፆታ አይነቶችን ያካትታል።



## ስርዓተ-ፆታ በስነ ልቦናዊ ቁስልና ተያያዥ ጭንቀት ላይ በሚካሄዱ ጥናቶች ውስጥ ለምን አስፈለገ?

- ፆታዊ/እና ስርዓተ-ፆታዊ ልዩነቶች በተለያዩ ቀደምት ስራዎች ተመዝግበው ይገኛሉ፤ ለምሳሌ አሰቃቂ አደጋዎችና ክስተቶች ሲያጋጥሙ፣ በስነ ልቦናዊ ቁስልና በተያያዥ ጭንቀት ምልክቶች ውስጥ ይጠቀሳሉ።
- ልዩነቶች በባሕላዊ እሴቶችና እምነቶች ሊቀረፁ ይችላሉ፤ ይህም የስርዓተ-ፆታ ልዩነት ያላቸውን ሰዎች በዓለም አቀፍ ጥናቶች ውስጥ ደህንነታቸውና ክብራቸውን ጠብቆ ለማሳተፍ ውስብስብ ጥያቄዎችን ያስነሳል።

## የተለመዱ ተግዳሮቶች እና የመፍትሄ ሃሳቦች፡

### ሕግ እና ስነ ምግባር

**ተግዳሮት፡** የስርዓተ-ፆታ ልዩነቶች በሁሉም የዓለማችን ክፍል አንድ አይነት አይደሉም። በምዕራባውያን እውቅና ያላቸው ከሁለት በላይ የሆኑ የስርዓተ-ፆታ አይነቶች በሌሎች አካባቢዎች እንደ ወንጀል ስለሚቆጠሩ ተሳታፊዎች ላይ ጥቃትና እስራት ሊደርስ ይችላል። የስነ ምግባር ገምጋሚ ቦርዶች ከሁለቱ ውጭ የሆኑ የፆታ አይነቶች በጥናት ውስጥ መካተትን ሊቃወሙ ይችላሉ።

**መፍትሔ፡** "መግለጽ አልፈልግም" የሚል አማራጭ መጠቀም፣ በጽሁፍ ምላሻቸውን እንዲገልጹ መፍቀድ፣ ቃለ መጠይቅን መጠቀም።

### መለኪያ

**ግድፈት፡** ሃገራችንን ጨምሮ በብዙ ቋንቋዎች በተፈጥሮ የተገኘን ፆታ እና የስርዓተ-ፆታ ማንነት ለመለየት ያስቸግራል።

**መፍትሔ፡** በተፈጥሮ የተገኝን ፆታ እና ከዛ ውጭ የሆኑ ስርዓተ ፆታ ማንነቶችን በግልጽ ማብራራት።

### ቁጥራዊ ቀመር

**ተግዳሮት፡** በፆታዊ ማንነት የመገለል ሁኔታ የገጠማቸው ሰዎች መረጃ በቁጥር የመቀመር አቅማቸው ዝቅተኛ ይሆናል።

**መፍትሔ፡** ሂሳባዊ (ቁጥር ነክ) ያልሆኑ መንገዶችን መጠቀም፤ የተለያዩ የስርዓተ ፆታ አይነቶችን ወደ ተመሳሳይ ክፍል በመመደብ የሂሳባዊ ቀመር አቅማቸውን መጨመር።

### ገለፃ አሰጣጥ

**ተግዳሮት፡** አጥኚዎች የተለያዩ ትርጉሞችን ሊሰጡ ይችላሉ፣ በጥሩ ሁኔታ የተገለጹ ጽሁፎች አላግባብ መገለልና መድልዎ ለመፈጸም እንደማጣቅሻ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

**መፍትሔ፡** የሚታተሙ ሰነዶች ግልጽ ትርጉሞችን መያዝ፣ የአቋም መግለጫ ሊኖራቸው ይገባል፣ እንዲሁም ጥናት አድራጊዎች ለዕውቀት ሽግግር ኃላፊነት መውሰድ አለባቸው ይህም የሚሰጡ ገለጻዎችን ቅርጽ ለማስያዝ ይረዳል።

በዚህ አርዕስት ዙርያ ያለዎትን ሃሳብ ለማጋራት ይፈልጋሉ? በዓለም አቀፍ ትብብር ለስነ ልቦና ቁስል እና ተያያዥ ጭንቀት ውስጥ የፆታ እና ስርዓት ፆታ ክፍልን ይቀላቀሉ።

ReACT Lab

Langevin, R., Beaudette, S., Wadji, D. L., Chabake, S. A., Gonzalez, C., Jenkins, D., … Spencer, R. (2024). Sex and gender considerations in cross-cultural traumatic stress studies. European Journal of Psychotraumatology, 15(1). https://doi.org/10.1080/20008066.2024.2408194

GLOBAL COLLABORATION on Traumatic Stress